# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 2 ቁጥር 75 የካቲት 5 ቀን 2013 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

# ኢዜማ በመቐለ፣ ማይካድራ፣ መተከል እና ኮንሶ በመጓዝ የሰበሰበውን መረጃ ይፋ አደረገ



# ኢዜማ በመቐለ፣ ማይካድራ፣ መተከል እና ኮንሶ በመጓዝ የሰበሰበውን መረጃ ይፋ አደረገ

የካቲት 5 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በከፍተኛ አመራሮች የሚመራ ቡድን ወደ መቐለ፣ ማይካድራ፣ ኮንሶ እና መተከል በከፍተኛ አመራሮች የተዋቀረ ልዑክ ቅኝት በማድረግ የሰበሰባቸውን መረጃዎች ሐሙስ የካቲት 04 ቀን 2013 ዓ.ም በኤልያና ሆቴል ለመገናኛ ብዙኃን ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል፡፡

በከፍተኛ አመራሮች የተዋቀረው የኢዜማ ልዑክ በመቐለ፣ ማይካድራ፣ ኮንሶ እና መተከል በመጓዝ የመስክ ምልከታ አድርጓል፡፡ ወደ መቐለ የተጓዘው ቡድን በመጠለያ ያሉ ወገኖች ተዟዙሮ ጎብኝቷል፡፡ ከፌዴራል መንግሥት ባለሥልጣናት፣ ከትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር እንዲሁም ከተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮች ጋር አሁን ስላለው ወቅታዊ ሁኔታ እና መፍትሔዎች ላይ ውይይት አድርጓል፡፡

ከትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ሙሉ ነጋ (ዶ/ር) ጋርም ውይይት ተደርጓል፡፡ በክልሉ አመራር የነበሩ ታዋቂ ፖለቲከኞችን፤ ታዋቂ ግለሰቦችን እና የሌሎች ፓርቲዎች አባላት በመዋቅሩ ውስጥ አካተው ቢጠቀሙባቸው ጥሩ እንደሚሆን በውይይቱ ወቅት የተጠቀሰ ሲሆን፤ ኢዜማ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደርን በዞን፣ በወረዳ፣ እና በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ አባላቶቹ በመመደብ ጊዜያዊ አስተዳደሩን ለማገዝ ዝግጁ መሆኑንም በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ጠቅሷል፡፡

ወደ መቐሌ የተጓዙት የኢዜማ ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ፣ በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ወደ መቐለ የተጓዙት የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሳይሆን ሕዝቡ ሰላም እና እርዳታ እንዲያገኝ ለማድረግ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በትግራይ ክልል የፀጥታ ችግር እንዳለና ተኩስ አሁንም ድረስ እንደሚሰማ፤ ሕዝቡ ስጋት ውስጥ እንዳለ መታዘባቸውን የጠቆሙት ሊቀመንበሩ፣ ሚዲያዎች በክልሉ ያለውን ሁኔታ ቦታ ድረስ በመሄድ መዘገብ እንደሚገባቸው ተናግረዋል፡፡

ማይካድራ የተጓዘው ቡድን ግጭቱን ተከትሎ በማይካድራ እና ሑመራ ከፍተኛ ሰብዓዊ ቀውስ፣ ሞት እና የሀብት ውድመት መከሰቱን የጠቆመ ሲሆን፤ የማይካድራው እልቂት የተጀመረው ጥቅምት 29 ቀን 2013 ዓ.ም ለጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም አጥቢያ መሆኑን እና እስከ ኅዳር 3 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ በነዋሪዎቹ ላይ እልቂት እንደተፈፀመ ከነዋሪዎች መረዳቱን ጠቁሟል፡፡ የሟቾቹ ቁጥር በሚመለከት ልዑክ ቡድኑ የተለያዩ መረጃዎችን የአካባቢው ነዋሪዎችን፣ ቀብር አስፈጻሚዎች እና የተጎጂ ቤተሰቦችን በማነጋገር መረጃ ለማሰባሰብ ሙከራ አድርጎ እንደነበር ጠቅሶ፤ የሟቾቹ ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ትክክለኛ ቁጥር ለማስቀመጥ እንደሚያዳግት ገልጿል፡፡

ቡድኑ ማይካድራን እና አካባቢውን በጎበኘበት ወቅት ነዋሪው በከባድ ፈተና ውስጥ እንደሚገኝ መረዳት መቻሉን የጠቀሰ ሲሆን፤ የደኅንነት ስጋት መኖር እና የመሠረተ ልማቶች ያለመኖር ነዋሪውን ለከፍተኛ ችግር እየዳረገው እንደሚገኝ በመግለጫው አመላክቷል፡፡





# ኢዜማ የፓርቲ ኮንፍረንሱን በቀጣይ ሳምንት እንደሚያካሄድ ገለፀ

የካቲት 5 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



ፎቶ:- ከፋይል

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከሰኞ የካቲት 08 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በ3 ደረጃ ባወቀራቸው የዘመቻ መዋቅሮቹ የምረጡኝ ዘመቻውን እንደሚጀምር አስታወቀ፡፡

ፓርቲው የካቲት 04 ቀን 2013 ዓ.ም በኤልያና ሆቴል በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ነው የምረጡኝ ዘመቻውን እንደሚጀምር ያስታወቀው፡፡ በምረጡኝ ዘመቻው ወቅት ኢትዮጵያ ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ እና አገሪቱን ወደ ተሻለ ደረጃ ሊወስዱ የሚችሉ ከሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች ይለዩኛል፣ የተሻሉ ናቸው ብሎ ያዘጋጃቸውን የመፍትሄ አማረጮች ይዞ በመቅረብ፣ ለሕዝብ የማስተዋወቅ እና ምረጡን ለማለት እንቅስቃሴ እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡

በሚቀጥሉት 100 ቀናት በየወረዳው የተዘረጉት የዘመቻ መዋቅሮች ምርጫ በሚደረግበት የአገሪቱ ክፍሎች ሁሉ የኢዜማን ሀሳቦች ለማስተዋወቅ እንደሚንቀሳቀሱ እና በክልል ደረጃ የተዘረጉት የዘመቻ መዋቅሮች እንደየክልሉ ሁኔታ በተለያየ መንገድ ኢዜማን ለማስተዋወቅ እንደሚንቀሳቀሱ በመግለጫው ተመልክቷል፡፡

ከምርጫው ዘመቻ ጋር በተያያዘም ኢዜማ በቀጣዩ ሳምንት ሁለት ዋና ዋና ክንውኖችን የሚያከናውን ሲሆን፤ የፓርቲው ኮንፍረንስም አርብ የካቲት 12 ቀን 2013 ዓ.ም ይካሄዳል። ኮንፈረንሱ ቀደም ብሎ መካሄድ የነበረበት መሆኑን የጠቀሰው ፓርቲው፣ የኮቪድ-19 ወረርሺኝ የተነሳ ለማራዘም መገደዱን አስታውቋል፡፡

የኢዜማ የፓርቲ ኮንፈረንስ ፓርቲው አባላትን ካደራጀባቸው የምርጫ ወረዳዎች አንድ ተወካይ የሚወከልበት እና ሦስት ዓመት አንዴ ከሚሰበሰበው የፓርቲው ጉባዔ ቀጥሎ ትልቁ ሥልጣን ያለው የፓርቲ አካል ሲሆን፤ ኢዜማ ከተመሰረተ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚደረገው ይህ ኮንፈረንስ የፓርቲውን ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ እና በጉባዔ የተመረጡ አካላትን የእስካሁን እንቅስቃሴ ሪፖርት በማዳመጥ ያፀድቃል ተብሎ ይጠበቃል። በተጨማሪም ኢዜማ በቀጣዩ ምርጫ የሚወዳደርባቸውን ፖሊሲዎች እና ማኒፌስቶ ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን የሚያፀድቅ ይሆናል፡፡

ሁለተኛው የኢዜማ ዐብይ ክንውን በሀገር አቀፍ ደረጃ የምርጫ ዘመቻ ማስጀመሪያ ዝግጅት ሲሆን ይህም ዝግጅት የካቲታ 13 ቀን 2013 ዓ.ም በግዮን ሆቴል ይደረጋል። በዚህ ዝግጅት ላይ ከመላው ሀገሪቱ ካሉት 435 የምርጫ ወረዳ መዋቅሮች የሚመጡ የፓርቲው የኮንፍረንስ አባላት ጨምሮ በአዲስ አባበ የሚገኙ አባለት እና ደጋፊዎቻችን የሚታደሙበት እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ኢዜማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ አባላት፣ ደጋፊዎች እና ፓርቲው በቀጣዩ ምርጫ ይዟቸው የቀረቡትን የመወዳደሪያ ሀሳቦች መስማት እና ዕጩዎችን መተዋወቅ የሚፈልጉ የከተማዋ ነዋሪዎች በሙሉ በዚህ የምርጫ ዘመቻ መክፈቻ ክንውን ላይ እንዲካፈሉ ግብዣውን አቅርቧል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)


የካቲት 05 ቀን 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ኢዜማ፣ በኤልያና ሆቴል ባዘጋጀው የፖሊሲ አውደ ጥናት ላይ የፖሊሲ ረቂቆቹን ለውይይት አቀረበ።

የካቲት 5 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)







የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በያዝነው ዓመት ግንቦት መጨረሻ ለሚደረገው ሀገር አቀፉ ምርጫ የአገራችንን ችግሮች በሂደት ይፈቱልኛል፤ ዜጎች የተሟላ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላሉ፤ ሁለንተናዊ፣ መሰረተ ሰፊና ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ የምጣኔ ኃብት ዕድገትና ልማት ለማምጣት ይረዳሉ፤ ማኅበራዊ ፍትህ ለማስፈን፤ ዘላቂ ልማትና ዋስትና ያለው ሰላም ለማረጋገጥ፣ እንደዚሁም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ-መንግሥትን በኢትዮጵያ ዕውን ለማድረግ ይረዳሉ ብሎ ያመነባቸውን 45 የፖሊሲ ሰነዶችና በሂደትም ፖሊሲዎቹን ለማስፈፀም የሚረዱ ስልቶች (strategies) ቀረፃ እያደረገ እንዳለ ይታወቃል፡፡

ፓርቲው እነዚህን ፖሊሲዎች ለባለድርሻ አካላት ይፋ በማድረግ ሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ ሐሙስ የካቲት 04 ቀን 2013 ዓ.ም እና አርብ የካቲት 05 ቀን 2013 ዓ.ም በኤልያና ሆቴል ባካሄደው የፖሊሲ አውደ ጥናት ላይ የግብርና ፖሊሲ፣ የመሬት ፖሊሲ፣ ምግብ ዋስትናና የሥርዓተ-መብል ፖሊሲ፣ የአደጋ ስጋት ቅነሳና አመራር ፖሊሲ እና የአርብቶ አደር ፖሊሲ ለውይይት ቀርበዋል ፡፡ ረቂቅ ፖሊሲዎቹ ላይ ባለሙያዎች አስተያየታቸውን የሰጡበት ሲሆን፤ ፖሊሲውን በመቅረፅ ሂደት ሚና የነበራቸው ምሁራንም ከባለሙያዎቹና ከአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ለተሰነዘረው ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ኢዜማ በፖለቲካ፤ በማኅበራዊና በምጣኔ ሀብት ዘርፍ ፖሊሲዎቹን የከፋፈለ ሲሆን በእነዚህ ዘርፎች ሥርም ከ40 በላይ ፖሊሲዎችን የፓርቲው አባል በሆኑና አባል ባልሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችን አሳታፊ ባደረገ መልኩ መቅረፅ ችሏል፡፡ ኢዜማ በማህበራዊ ዘርፍ በሚቀርፃቸው ፖሊሲዎች የድህነትና አለእኩልነት (poverty & inequality) ምንጭ የሆኑትን ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች በመቀነስ፤ ብሎም ከምንጫቸው በማድረቅ የኢትዮጵያውያንን ኑሮ ለማሻሻል ይሰራል። ፖሊሲዎች ዜጎች የዕኩል መብት፣ የዕኩል ዕድልና የዕኩል አያያዝ (equal right, equal opportunity, & equal treatment) ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማስቻል ከድህነትና አለእኩልነት የተላቀቀ፤ እንደዚሁም ከስጋት ነፃ የሆነና ተረጋግቶ የሚኖር፤ በአካባቢያዊና አገራዊ የምጣኔ ሀብትና ማኅበረ-ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት የሚሳተፍና በተሳትፎውና ጥረቱ ልክ ተጠቃሚ የሚሆን ማኅበረሰብ መፍጠርን ግብ ያደረጉ ናቸው፡፡ የኢዜማ የምጣኔ ሀብት ዘርፍ ፖሊሲዎች ፈጣን፣ መሰረተ-ሰፊና የሀገሪቷን ሕዝቦች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ የሚተገበሩ ዝርዝር ፖሊሲዎች ናቸው። ውጤታማ ፖሊሲዎችን በመተግበር የሥራ አጥ ቁጥር እንዲቀንስና በግል ስንፍና ካልሆነ በስተቀር ዕድሜው ለሥራ የደረሰ ኢትዮጵያዊ ሁሉ አማራጭ ከማጣት የተነሳ ስደት ውስጥ መግባት ሳያስፈልግ በቂ የሥራ ዕድል በአገር ቤት የሚመቻቸበት፤ የተረጋጋ የገበያ ስርዓት በተለይም የመሰረታዊ ፍጆታ ሸቀጦች ዋጋ ከግሽበትም ሆነ ከንረት የፀዳ እንዲሆንና የዳበረ አገር-በቀል የግል ክፍለ-ኢኮኖሚ ዕውን የሚሆንበት ሥርዓት መዘርጋትን ግብ ያደረጉ ፖሊሲዎች እየተዘጋጁ ነው። በኢኮኖሚው ዘርፍ በሚሰራ ውጤታማ የፖሊሲ ቀረፃና አተገባበር የህብረተሰቡን መሰረታዊ ፍጆታዎች በሐገር ውስጥ በማምረት የኑሮ ውድነትን መቀነስ እንደሚቻል ፓርቲው በፖሊሲዎቹ አመላክቷል፡፡

በፖለቲካው ዘርፍ ያሉት ፖሊሲዎች በኢትዮጵያ የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት እንዲጠናከር፣ የመገናኛ ብዙኃንና ሲቪል ማኅበራት እንቅስቃሴ እንዲጎለብት፤ የፌደራል ሥርዓታችን እንዲዳብርና የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶችና ደህንነት ሙሉ ለሙሉ ለማክበር በሚያስችልና ልማትንና አስተዳደርን በሚያቀላጥፍ መልኩ እንዲደራጅ ለማድረግ፤ ሥልጣን ወደታችኛው እርከን የሚወርድበትና ያልተማከለ አስተዳደር በትክክልም ተግባራዊ የሚሆንበትን እውነተኛ ፌደራላዊ ስርዓት እንዲፈጠር የሚተገበሩ ፖሊሲዎች ናቸው። ፖሊሲዎቹ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ የፍርድ ቤቶች ነፃነት፣ የአገር ሰላምና የግዛት አንድነት የሚረጋገጥበት እና ሕዝቡ የሉዑላዊ የስልጣን ባለቤትነቱ ዋስትና የሚያገኝበትን ግብ የሚያሳኩ ናቸው፡፡ በዚህ ዘርፍ በሚተገበሩት ፖሊሲዎች የፖለቲካ ምህዳሩን በማስፋትና የመንግሥትን ስልጣን ሕገ-መንግሥታዊና በህግ የተገደበ በማድረግ ዜጎች በነቃ ተሳትፏቸው ዕውን የሚያደርጉት ሲሆን ይህም የአገሪቱ የሕዝባዊ-መንግስት ምስረታ ጥያቄን ለመመለስ የተደረገው የ50 ዓመት ትግል ለማሳካትን እንደ ግብ የያዙ ፖሊሲዎች ናቸው፡፡

በሁሉም ዘርፍ ግብአት ሲሰበሰብባቸውና ሲቀረፁ የቆዩት ፖሊሲዎች፣ የኢዜማ ኮንፍረንስ ካፀደቃቸው በኋላ ለሕዝብ ይፋ ይሆናሉ፡፡ የፓርቲው ኮንፍረንስም አርብ የካቲት 12 ቀን 2013 ዓ.ም የሚካሄድ ይሆናል፡፡





# ኢዜማ በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ ዕጩ ተመራጮች ስልጠና መስጠት ጀመረ።

የካቲት 5 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በ2013 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሕዝብ ተወካዮች እና ለክልል ምክር ቤት የሚወዳደሩ ዕጩ ተመራጮችን ማሰልጠን ጀመረ፡፡

ኢዜማ በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ አባላቶቹ ከየካቲት 5 እስከ የካቲት 6 ቀን 2013 ዓ.ም ለዕጩ ተመራጮች፣ ለየምርጫ ወረዳው ሊቀመንበር፣ በምርጫው ቅስቀሳ ላይ ተሳትፎ ለሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት ከየካቲት 8 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ለሚጀመረው ምርጫ ቅስቀሳ የኢዜማ ምርጫ ወረዳ ቅስቀሳውን እንዴት መወጣት እንደሚችል፣ ቁጥጥሩ እንዴት መሆን እንደሚገባው፤ ምርጫውን የሚመራው የወረዳው ምርጫ ኮሚቴ ሥራውና ተግባሩ ምን እንደሆነ የሚያሳውቅ ሥልጠና በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ከምርጫ ወረዳዎቹ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ የተሰራው ዘመቻው የሚመራበት ፍኖተ ካርታ በስልጠናው ላይ በመስጠት በፍኖተ ካርታው ላይ ውይይት እንደሚደረግ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በየዞኑ ስልጠና የሚሰጣቸው በምርጫው ላይ ዋና ኃላፊነት ያለባቸውን ሲሆኑ፤ ስልጠናውን የሰለጠኑት ኢዜማ ባስቀመጠው ስብጥር መሠረት ኮሚቴ በማዋቀር የወረዳው አባላት እና ሥራ አስፋጻሚውን አካተው የሰለጠኑትን ስልጠና ያሰለጥናሉ፡፡

‹‹ኢዜማ ዕጩ ባላስመረጠባቸው ምርጫ ወረዳዎች ስልጠናውን በምን ዓይነት መልኩ ሊሰጥ አስቧል?›› በማለት የዜጎች መድረክ ጠይቃ ዕጩ ያልመረጡ ወረዳዎች በቅርቡ እንዲመርጡ በማድረግ ስልጠናው እንደሚሰጥ፣ በተመሳሳይ ዕጩ ተመራጮችን መርጠው አዳራሽ በማጣታቸው ምክንያት ስልጠና መስጠት ያልተቻለባቸው ምርጫ



ወረዳዎች፤ በቀጣዩ ጊዜያት እነሱን ተደራሽ የሚያደርግ ስልጠና ተዘጋጅቶ እንደሚሰጥ የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል፡፡

በአዲስ አበባ ለሚገኙ ዕጩ ተመራጮች ጥር 29 እና ጥር 30 ቀን 2013 ዓ.ም ስልጠናው መሰጠቱ የሚታወስ ነው፡፡

# በባህር ዳር አንድ ሊትር ቤንዚን ከ60 እስከ 70 ብር ድረስ በጥቁር ገበያ እየተሸጠ ይገኛል

የካቲት 5 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ባህር ዳር ምርጫ ወረዳ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ መንግሥቱ አማረ፣ በባህር ዳር በተከሰተ የነዳጅ እጥረት የተነሳ ነዳጅ በጥቁር ገበያ እየተሸጠ እንደሚገኝ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡



በከተማው ለብዙ ጊዜያት የነዳጅ እጥረት ይስተዋል እንደነበር የጠቀሱት ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፣ ያለፉት አንድ ሳምንት ግን ከእጥረት ባለፈ ነዳጅ በከተማው ውስጥ እንደጠፋና በጥቁር ገበያ እየተሸጠ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡ በጥቁር ገበያም አንድ ሊትር ቤንዚን ከ60 እስከ 70 ብር እየተሸጠ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

በነዳጅ መጥፋት የተነሳ ከፍተኛ የትራንስፖርት ችግር እንደተከሰተ እና በእቃዎች ላይም የዋጋ ንረት እንዳስከተለ የጠቀሱት መንግሥቱ አማረ፣ የነዳጁ እጥረት በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ ሕዝቡ ለከፍተኛ የማኅበራዊ ቀውስ እንደሚዳረግ አስረድተዋል፡፡ እጥረቱ በከተማው የንግድ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማስከተል ባለፈም መሠረታዊ የሚባሉ የምግብ ፍጆታዎች ዋጋ እንዲያሻቅብ ማድረጉን ጠቁመዋል፡፡ የነዳጅ እጥረቱ በባህር ዳር መከሰት ከጀመረ አንድ ዓመት ያስቆጠረ እንደሆነ የጠቀሱት የባህር ዳር ምርጫ ወረዳ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፣ ባለፈው አንድ ሳምንት ግን ነዳጅ እጥረት ከመከሰት ባለፈ ሙሉ ለሙሉ መጥፋቱንና ከጥቁር ገበያ ውጪ ነዳጅ ማግኘት እንደማይቻል ተናግረዋል፡
የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከጥር 30 ቀን 2013 ጀምሮ እስከ የካቲት 30 ቀን 2013 ባሉት ቀናት ውስጥ የነዳጅ ምርቶች ችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ላይ ክለሳ መደረጉን ማስታወቁ አይዘነጋም፡፡ የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ ዋጋ ጭማሪው ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በመላው አገሪቱ በሚገኙ አካባቢዎች እንደ የርቀታቸው መጠን ከጥር 30 ቀን 2013 ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚሆን መግለጹ ይታወሳል፡፡